# አዴኃን በጎጃም ክፍለ ሀገር አዴት ወረዳ ጥቃት ሰነዘረ፡፡

April 11, 2018

የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ(አዴኃን) ትላንት ምሽት ሌሊት 6 ሰዓት10 ደቂቃ ላይ በጎጃም ክፍለ ሀገር አዴት ወረዳ ጥቃት ሰነዘረ፡፡

ድርጊቱ የተፈፀመው አዴት ከተማ ጋፋት ሚካኤል ሰፈር ሲሆን በአዴት ዙሪያ ወረዳ ማለት በይልማና ዴንሳ ወረዳ የፓሊስ አዛዥ እና የወረዳው የኮማንድ ፓስት ተጠሪ በሆነው በኮማንደር በሬ አየነው መኖሪያ ቤት ላይ ነው፡፡

ሰዓቱም ከሌሊቱ 6:10 ሲሆን የክሳሺንኮቭ ጥይት ድብደባ እና በእጅ ቦንብ ነው ጥቃቱ የተሰነዘረው፡፡ በጥቃቱ በሰው ላይ ምንም የደረሰ ጉዳት የለም፡፡በኮማንደሪ መኖሪያ ቤት ላይ ጉዳት ሰርሶበታል፡፡

ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ ታጋዮቹ ቦታው ከለቀቁ በኋላ የከተማው ፓሊስ አዛዥ ኢንስፔክተር አሰፋ ወንድማገኝ እና እሱ የሚመራቸው ብዛት ያለው የፓሊስ ኃይል ይዘው ከተማው በተኩስ ሲያምሱት ፣ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እና ታዛቢ የብዙ ሰዎችን ቤት ሲፈትሹ ሲበረበሩ አንግተዋል፡፡በተጨማሪም ብዙ ሰዎችን አስረዋል፡፡

ከእዚህ ቀደም የዛሬ አንድ ወር ጥቃት የተሰነዘረበት ኮማንደር በሬ አየነው እና ኢንስፔክተር አሰፋ ወንድማገኝ ለደህንነቶቹ አሳልፈው የሰጡት የአዴት ከተማ ልጅ የሆነው ገበየሁ ፈንታሁን በማዕከላዊ ፡




በድብደባ ብዛት ህይወቱ አልፋል፡